**የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ምዕመናን ዓለም አቀፍ ማሕበር**
**WORLD ASSOCIATION OF PARISHIONERS OF E.O.T. CHURCH**

ቁጥር: ዐሰ/212/05
ቀን: 27/ 1/2005 ዓ.ም

# ግልጽ ደብዳቤ

"የትዕግሥት እና የመጽናናት አምላክ እግዚአብሔር እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ፈቃድ
እርስ በእርሳችን አንድ ሐሣብ መሆንን ይስጠን። ሁላችን አንድ ሆነን በአንድ አፍ በጌታችን
በኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሄርን እናመስግነው ዘንድ።" ሮሜ 15:51

ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ
ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ
<u>ዋሽንግተን ዲ.ሲ.</u>

ለብፁዕ አቡነ ናትናኤል
አቃቤ መንበረ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ እና
የአርሲ አገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ
<u>አዲስ አበባ</u>

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
ካህናት እና ምዕመናን
<u>በያሉበት</u>

ዋና ጽሕፈት ቤቱን በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ አድርጎ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ምዕመናን ዓለም አቀፍ ማኅበር፤ ከሁሉ በማስቀደም፤ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖትን ነፍስ ሁሉን አድራጊ የሆነው ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ከቅዱሳኑ ጋር ያሳርፋት ዘንድ ያለውን ጽኑ ምኞቱን ይገልጣል።

በመቀጠልም፤ በቤተክርስቲያናችን ውስጥ የተከሰተው መከፋፈል ይበልጥ እየተውሰበሰበ በመሄድ ላይ የሚገኘው በውግዘቱ ምክንያት መሆኑን አመልክተን ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ እና ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ጽፈነው የነበረውን ደብዳቤ ማስታወስ ይፈቀድልን።

4002 Blacksmith Drive, Garland, TX 75044 - www.eotcipc.org
miimenan@yahoo.com; (214)703 9022

ቅዱስነቶቻቸው ፈቃዳቸው ሆኖ በስጡን ቀጠሮዎች የወከልናቸው የማኅበራችን አባላት ከሁለቱም ቅድሳን አባቶች ጋር በአካል ተገናኝተው ደብዳቤውን ከማቅረባቸውም ባሻገር፤ ጉዳዩን በቃል ጭምር እንዲያስረዱ ዕድል ተሰጥቷቸው ነበር። በዚያ ደብዳቤያችን አማካይነት፦

ሀ. የቤተክርስቲያኗን ምዕመናን ከገጠሙን ዘርፈ ብዙ ፈተናዎች ሁሉ እጅግ የሚያሳስበን፤ አንድ ከሚያደርጉን ይልቅ የሚከፋፍሉን ነገሮች እየጨመሩና እየተውሰበሰቡ በመሄድ ላይ መገኘታቸውን፤

ለ. ሐዋርያዊት፤ጥንታዊት፤ታሪካዊት፤ብሔራዊት እና ሲኖዶሳዊት የሆነችው ቅድስት ቤተክርስቲያናችን፤ አንድነቷን የተፈታተኑ ችግሮችን እየፈታች እና ዶግማዋን፤ ቀኖናዋን እና ሥርዓቷን እየጠበቀች፤ የደነገገቻቸውንም ሕጎች አክብራ እያስከበረች እስካሁኑ ትውልድ መዝለቅ መቻሏን፤

ሐ. በአሁኑ ዘመን ግን፤ በአገር ውስጥ እና በውጭው ዓለም የሚገኙት ቅዱሳን እና ብፁዓን አባቶቻችን ከመለያየት አልፈው እስከ መወጋገዝ በመድረሳቸው፤ ሥርዓታቷ እና ሕግጋቷ እየተጣሱ ታሪካዊ አንድነቷ ሊፈርስ በሚችልበት አደገኛ ጎዳና ስታዘግም መስተዋሏን፤ እና

መ. ሌሎች ተዛማጅ ችግሮችንም በመዘርዝር፤ ከቤተክርስቲያናችን ችግሮች ሁሉ <u>*የውግዘቱ*</u> ጉዳይ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት <u>*እንዲሻርልን*</u> እና በየአካባቢያችን በሚገኙት እና ወደፊትም በሚመደቡት ብፁዓን አባቶች፤ ጐራ ሳንለይ መባረክ እና መመራት የምንችልባት ዕለት እንድትብትልን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስን እና ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስን ለምነን ነበር።

ለዚህ ደብዳቤያችን በጎ ምላሽ እናገኝ ዘንድ እየፀለይን የተወሰኑ ወራት ካሳለፍን በኋላ፤ ባላሰብነው እና ባልጠበቅነው ሁኔታ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ከዚህ ዓለም በድንገት መለየታቸውን ተረድተን ደንግጠናል። አዝነናል። እንደየአቅማችንም ለቅዱስነታቸው ነፍስ ፀልየናል። የቅዱስነታቸውን ዕረፍት ተከትሎ ኢትዮጵያን በፕሬዚዳንትነት እና በጠቅላይ ሚኒስትርነት ለ21 ዓመታት የመሩትን የክቡር አቶ መለስ ዜናዊን ህልፈተ ህይወት ስለሰማን፤ ሐዘኑ ጋብ እስኪል ድረስ ይህንን ደብዳቤያችንን ለማዘግየት ተገድደን ጠብቀናል።

በዚሁ ጊዜ ውስጥ ግን፤ በአገራችን ውስጥም ሆነ ከአገራችን ውጭ የሚገኙት አባቶቻችን ለቤተክርስቲያኗ ሰላም እና አንድነት ቅድሚያ ትኩረት ሰጥተው በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ዋናውን የአመራር ችግሯን ለመፍታት ቆራጥ አቋም ይዘው በመፀለይ ላይ መሆናቸውን ስለተረዳን በእጅጉ ተጽናንተናል።

ቤተክርስቲያናችን አገራዊ እንደ መሆኗ መጠን፤ በአገራችን ውስጥ የሚከሰቱ ማኅበራዊ፤ ፖለቲካዊ፤ ኤኮኖሚያዊ እና ባህላዊ ዕውንታዎች ሁሉ በቤተክርስቲያኗ ላይ የየበኩላቸውን አዎንታዊም ሆኑ አሉታዊ ተጽእኖዎች እንደሚያሳድሩ ከሩቁም ሆነ ከቅርቡ ታሪካችን እንረዳለን።

የቤተክርስቲያናችንን ችግሮች ለመፍታት መንፈሳዊ አባቶቻችን በትዕግሥት፤ በእርቀ አስተዋይነት፤ በቅንነት እና በዕውነተኛነት ቆርጠው እስከተነሱ ድረስ፤ እግዚአብሔርም ስለሚጨመርበት፤የሚሳናቸው ነገር ይኖራል ብለን አንጠራጠርም።

በቤተክርስቲያናችን ላይ የተጋረጠው ችግር በተለያዩ የታሪክ ወቅቶች የኦርየንታልንም ሆነ የምሥራቅን ኦርቶዶክስ አብያተክርስትያናት እንደተፈታተነና በሂደትም መፍትሔ እንደተገኘለት ከአባቶቻችን የተሰወረ አይደለም።

ፋሽስት ጣልያን አገራችንን በወረረችበት ዘመን ተከስቶ የነበረው የሰላም እና አንድነት ችግር እና የችግሩ አፈታት የቤተክርስቲያናችን ታሪክ አካል ስለሆነ በመጠኑም ቢሆን የመፍትሔ ሐሳብ ሊጠቅም ይችላል ብለን እንገምታለን።



4002 Blacksmith Drive, Garland, TX 75044 - www.eotcipc.org
miimenan@yahoo.com; (214)703 9022

በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ የሚገኙት የመንፈስ ቅዱስ አባቶቻችን የሚመሩት ሐዋርያት በሠሩት ቀኖና እንደ መሆኑ መጠን፤ በመካከላቸው ሰላም እና አንድነትን ለማስፈን የሚያደርጉት ጥረት፤ ሐዋርያት በደነገጉት ቀኖና መሰረት እስከ ተከናወነ ድረስ የበረታ እንቅፋት ይገጥመዋል ብሎ መስጋት አይቻልም።

በተጨማሪም፤ ከማናቸውም ሌላ ስሜት ይልቅ በፍጹም መንፈሳዊ አመለካከት ጸንቶ ለቅድስት ቤተክርስቲያናችን የአንድነት ችግር በአገራችን የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 398 እና 399 ባገኘችው መብትና ሕጋዊ ሰውነት፤ በፍትሐ ነገሥቱ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 77 እና 78 በተደነገገው ሥርዓት እና እንደዚሁም ቅዱስ ሲኖዶስ ባወጣው ሕገ ቤተክርስቲያን ላይ ተመሥርቶ እና ችግሩንም ከተጨባጭ መረጃዎች ጋር አገናዝቦ መፍትሔ መሻቱ፤ ፍትሓዊ እና አዛላቂ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ይረዳል ብለን እናምናለን።

ጉዳዩ አሳስቦን እላይ በጠቀስናቸው እና በሌሎች ተዛማጅ ሁኔታዎችም ላይ ሐሣብ ስንለዋወጥ ከቆየን በኋላ፤ የተገለጡልንን ፍሬ ነገሮች ለመንፈሳዊ አባቶቻችን ማሳወቅ ይገባናል ብለን ስለአመንን፤ ከዚህ በታች የዘረዘርናቸውን ሐሳቦች በታላቅ አከብሮት እናቀርባለን።

1. ለሰላም እና አንድነቱ ችግር ፍቺ የሚቋጠረው ሐሣብ፤ የቤተክርስቲያኗን ደህንነት አስቀድሞ፤ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ችግር እንዳይገጥማት ፅኑ መሠረት የሚጥል ቢሆን፤

2. አገር ውስጥ እና ከአገር ውጭ የሚገኙት አባቶቻችን የቤተክርስቲያናችንን አንድነት ለማደስ የሚያደርጉት ጥረት ይቀል ዘንድ፤ አለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ ውግዘቱ ቅድሚያ ተሰጥቶት ቢነሳ፤

3. ለሰላም እና አንድነቱ ችግር አስተማማኝ መፍትሔ እስኪገኝ ድረስ በአገር ውስጥ የሚገኘው ቅዱስ ሲኖዶስ አዲስ ፓትርያርክ ከመምረጥ ቢታገስ፤

4. ከቤተክርስቲያን ሰላም እና አንድነት የበለጠ ጉዳይ ስለሌለ፤ እግዚአብሔር በሰጠው ዕድል ተጠቅሞ አራተኛውን ፕትርያርክ ወደ መንበረ ተክለሃይማኖት የመመለሱ ጉዳይ ትኩረት ቢያገኝ፤

5. የአራተኛውን ፕትርያርክ እድሜ እና አጠቃላይ ሁኔታ እግምት ውስጥ በማስገባት፤ በእሳቸው እና በቅዱስ ሲኖዶሱ ምርጫ በዕምነቱ፤ በዕውቀቱ እና በሥራ ልምዱ ብቃት ያለው አባት በእንደራሴነት መድቦ የአስተዳደር ተግባራትን ማካሄድ የሚቻልበት ሁኔታ ቢፈጠር፤

6. ስለአራተኛው ፓትርያርክ ወደ ቀድሞ መንበራቸው መመለስ እና ከተመለሱ በኋላም ስለሚኖረው አሠራር በስደት የሚገኙት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ እና በእሳቸው የሚመራው ቅዱስ ሲኖዶስ ድርሻ ተግባራቸውን ቢፈጽሙ፤

7. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግሥት ለአራተኛው ፓትርያርክ ወደ መንበራችው መመለስ ይሁንታ ቢሰጥ እና ተመልሰው በመንበረ ተክለ ሃይማኖት ይቀመጡ ዘንድም አስፈላጊውን ድጋፍ እና ትብብር ቢያደርግ፤ እና

8. በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ የሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ካህናት እና ምዕመናን ለእርቀ ሰላሙ ውጤታማነት የሚጠበቅባቸውን ሁሉ በንቃት ቢያከናውኑ።



4002 Blacksmith Drive, Garland, TX 75044 - www.eotcipc.org
miimenan@yahoo.com; (214)703 9022

በመጨረሻም፤ ይህን ግልጥ ድብዳቤያችንን መቋጨት የምንፈልገው፤ በሺህ ዓመታት የሚዘከር ታሪክ ያስመዘገበችው ቤተክርስቲያናችን ከአጠቃላዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ውስጥ የነበራት የመቶኛ ድርሻ እያሽቆለቆለ በመሄድ ላይ መገኘቱ የታላቅ ድክመት እና ችግር ምልክት መሆኑን በማሳሰብ ነው።

ቸሩ ፈጣሪያችንን የተጣላው ታርቆ እና የተለያየው አንድ ሆኖ፤ በአሐቲ ቅድስት ቤተክርስቲያን ውስጥ፤ በአንድ ቅዱስ ሲኖዶስ መንፈሳዊ አመራር ሥር ሆነን አንድ አምላክን የምናመልክበትን ቀን ያቀርብልን ዘንድ እንለምነዋለን።

ወስብሃት ለእግዚአብሔር።

ይሥሐቅ ከፍሌ
የቦርዱ ሰብሳቢ

ግልባጭ:

ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የተወካዮች ምክር ቤት

ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሚኒስትሮች ምክር ቤት

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት

አዲስ አበባ

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት

ኦክላንድ፤ ካልፎርንያ



4002 Blacksmith Drive, Garland, TX 75044 - www.eotcipc.org
miimenan@yahoo.com; (214)703 9022